# <u>በዓረና የተጠራው የመቀሌ ሕዝባዊ ስብሰባ እና አንድምታው</u>

**(ከገብሩ ዐሥራት)**

በቅርቡ ትግራይ ውስጥ በተቃዋሚነት በሚንቀሳቀሰው እና «ዓረና ትግራይ ለዴሞክራሲ እና ሊዓላዊነት» በሚል በሚታወቀው ፓርቲ ታላቅ ሕዝባዊ ስብሰባ ተካሄዶ ነበር፡፡ ፓርቲው ከተመሰረተ ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ በትግራይ (መቀሌ) ጥር 24 ቀን 2001 ዓ.ም የተካሄደው ስብሰባ የተለያዩ ብዙኀን መገናኛን ቀልብ ስቦ ስንብቷል፤ የስብሰባውን ጥሪ በብዙኀን መገናኛ አማካይነት ያዳመጡ ወገኖችም የተለያዩ ጥያቄዎችን ከማንሣት አልተቆጠቡም፡፡ ዕውን የትግራይ ሕዝብ ከህ.ወ.ሓ.ት ሌላ አማራጮችን ይፈልጋልን? ዓረና ትግራይ ውስጥ ይህን መሰል ታላቅ ሕዝባዊ ስብሰባ ማድረግ ከቻለ የፓለቲካ ምኅዳሩ እንዴት ጠባብ ነው ሲባል ይችላል? « ሰላማዊ እና ሕጋዊ የትግል አገባብ አይቻልም» የሚሉትስ ጉዳዩን እንዴት ይመለከቱታል? የሚሉ ጥያቄዎች ሲሰነዘሩ ሰንብተዋል፡፡

**I ዕንቅፋት ይወገዳል፤ ችግርም ይፈታል!**

የመቀሌ ስብሰባ እንዲሁ በቀላሉ የተካሄደ አልነበረም፡፡ ብዙ ዕንቅፋቶች እና ውጣ ውረዶች አጋጥመውታል፡፡ በአገራችን ሕገ መንግሥት እና ሕጎች መሰረት ስብሰባ መጥራት እና ማደራጀት የሚፈቀድ ቢኾንም ያለው ውጣ ወረድ እና ጋሬጣ ግን እጅግ ከባድ ነው፡፡ ዓረና ስብሰባ ጠይቆ ለማስፈቀድ በ10 ቀናት በላይ ወስዶበታል፡፡ መኪና እና ድምጽ ማጉያ ተከራይቶ ሕዝቡ በስብሰባወ እንዲገኝ ለማወጅ ሲሞክርም በጸጥታ ኀይሎች ተከልክሏል፡፡ የማስተዋውቁ የነበሩትን የዓረና ስዎች አግተዋል፡፡በስብሰባው ዋዜማ ማለትም ቅዳሜ ጥር 23 ቀን ከሰዓት በኀላ በአዳራሹ የተተከለው ድምጽ ማጉያ ተፈቶ ተነቅሏል፡፡

በስብሰባው ቀን ሕዝቡ በየቀበሌው ሌላ ስብሰባ እንዲያደርግ እና በነቂስ እንዲወጣ እንዲያውም ሰብሰባው በልማት ዙሪያ የሚመክር ስለኾነ ማንም መቅረት እንደሌለበት ተላለፏል፡፡ ስብሰባው ከመካሄዱ በፊት የህ.ዉ.ሓ.ት መሠረታዊ ድርጅት አመራር አባላትም መክረዋል፤ ስብሰባውን እንዴት ማጨናገፍ እና መበተን እንደሚቻልም በጥልቀት ተመክሯል፡፡ በርካታ የህ.ወ.ሓ.ት አባላት « ስብሰባችኹን ለማደናቀፍ ስለ ታቀደ ጥንቃቄ አድርጉ» በሚል መልእክት ለዓረና በምስጢር

ያስተላልፋ ነበር፤ ዓረናም በተቻለ መጠን ይህን ለመቋቋም ዝግጅት በማድረጉ ስብሰባው እንዳይካሄድ የተደቀኑበትን ዕንቅፋቶች አስወግዶ እሑድ ጥር 24 ቀን ከጠዋሩ ሁለት ሰዓት ላይ ሕዝቡ በይበልጥ ደግሞ ወጣቱ በከፍተኛ ቁጥር በተገኘበት ኹኔታ ሕዝባዊ ስብሰባውን በድምቀት አካሂዷል።

**II ለውጥ የናፈቀ ሕዝብ!**

በታላቅ ጭብጨባ እና አክብሮት የዓረናን ተወካዮች የተቀበለው ተሰብሳቢ በንባብ የተሰማውን የፓርቲውን ኘሮግራም መግለጫ በጥሞና ካዳመጠ በኋላ የተለያዩ ጥያቄዎችን አንሥቶ ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል። ጥያቄዎቹ ፓሊሲን እና አሰራርን ያካተቱ ሲኾኑ አልፎ አልፎም በግለሰቦች በተለይ ( በሊቀ መንበሩ በአቶ ገብሩ ዐሥራት) እና ህ.ወ.ሓ.ት አፈንጋጭ በሚላቸው ላይ ያተኮሩ ነበሩ። ለአብነት ከቀረቡት በርካታ ጥያቄዎች ውስጥ በአጽንዖ የቀረቡት 1ኛ/ እናንተን ከህ.ወ.ሓ.ት/ኢሕአዴግ የሚለዩዋችሁ መሰረታዊ አቋሞች የትኞቹ ናቸው 2ኛ/ የባሕር በር ባለቤትነት ትያቄ ማንሣት ጦርነት ማወጅ አይኾንም ወይ የሚሉ ይገኙበታል።

ከመድረኩ በተሰጠው መልስ ዋነኛው ልዮነታች ህ.ወ.ሓ.ት/ኢሕአዴግ የአገዛዙ መሰረታዊ አቋም አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚል ነው ። አብዮታዊ ዴሞክራሲ የአንድ ፓርቲን ፈላጭ ቆራጭነት ለማረጋገጥ ኢሕአዴግ የመረጠው ርእዮተ ዓለማዊ አቅጣጫ ሲሆን አረና ግን መሰረታዊ የዜጎችን ዴሞክራሳዊ መብቶች ያረጋፈግጣል የሚለውን ሊበራል አስተሳሰብ ያራምዳል። በመኾኑም የመድበለ ፓርቲ ስርዓት እውን የሚሆንበትበን የፓለቲካ ስርዓት ለማስፈን ይታገላል፤ ተቃዋሚዎችን በተፎካካሪነት እንጂ በጠላትነት አይፈርጅም፤ ፍትሐዊ የኢኮኖሚ አቅጣጫን ይከተላል። ከዚህም ሌላ በኢትዮጵያ ልማት እና ለጸጥታዋ አስፈላጊ ነው የሚለውን የባህር በር ባለቤትነት ለማጋገጥ በሕጋዊ እና ሰላማዊ አገባብ ትግሉን እንደሚቀጥል ገልጧል። ይህን አቋሙን ለማስረገጥ ሕጋዊ መነሻዎችን በሚያብራራበት ጊዜ ጥቂት ሰዎች ሥነ ሥርዐት በማለት ስብሰባውን ለማወክ ሞክረዋል። ኾኖም ተሰብሳቢው ባደረገው ጨዋነት የተሞላበት እንቅስቃሴ ሙከራቸው ሊከፈሽፍ ችሏል። በመኾኑም ውይይቱ ቀጥሎ የኢትዮጵያ የባህል በር ባለቤትነት መብት ጥያቄ የኢትዮጵያን ሊዓላዊነት እና ጥቅም የሚያስከብር እንጂ ጦርነት የሚያውጅ ስላልኾነ በኘሮግራማችን ውስጥ አካትተን እንቀጥልበታልን የሚለውን ሐሳብ ሲቀርብ ቤቱ በጭብጨባ ተቀብሎታል። ከዚህ ሌላ ገዥው ፓርቲ ቢ.ፒ.አርን በመተግበር ሂደት ስለማከተለው አቅጣጫ ጥያቄ

ቀርቦ ዓረና  በጉዳዮ ላይ የመንግሥትን  አያያዝ በመኮነን፣ የመንግስት ሠራተኛ የማንኛውም ፓለቲካ ፓርቲ አባል ቢኾንም  የሥራ ውጤት  መመዘኛው ግን ሞያዊ ዕውቀቱ እና  ብቃቱ  መኾን እንዳለበት አቋሙን ግልጽ  አድርጓል፡፡
የመቀሌ ሕዝባዊ ስብሰባ በትክክል  የሕዝቡን  ፍላጎት ያንጸባረቀ ነበር፡፡ ገዢው  ፓርቲ «ትግራይ ከአንድ  ፓርቲ  በላይ ለመሸከም  ስለማይችል ከአንድ ፓርቲ በላይ አያስልገውም»  ቢልም  ሕዝቡ አማራጭ  እንዳሚፈልግ  ጫናዎችን በመቋቋም፣ ድምፁን አሰምቷል፡፡ የትግራይ ሕዝብ እንደሌላው  የኢትዮጵያ  ሕዝብ ሁሉ ሙስና፣ ብልሹ አስተዳደር ኢ- ፍትሐዊ እና ኢ- ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ተወግዶ በምትኩ ፍትሕ እና  ዴሞክራሲ እንዲደፍን ይፈልጋል፡፡  አንድ ሥርዐት አንዱን የኅብረተሰብ ክፍል እና  አንድን  አካባቢ ጠቅሞ ሌላውን ሊጎዳ አይችልም፡፡ ፍትሕ ካለ ለሁሉም የሚዳረስ ሲኾን  አፈና ካለም ሁሉንም የሚነካ ነው፤ በመኾኑም  የትግራይ ሕዝብም የሥርዐቱ  ሰለባ መኾኑ፡፡ ሁሉንም በዝርዝር ለማቅረብ ባይቻልም የተወሰኑትን መዳሰስ ግን ተገቢ ይኾናል፡፡

## <u>1ኛ. የትግራይ ሕዝብ አማራጭ  የማግኘት ጥማት፤</u>

የትግራይ ሕዝብ ከውጭ የሚመለከቱ  ወገኖች ህ.ወ.ሓ.ትን እና የትግራይ ኅብረተሰብን አንድ አድርገው ይመለከታሉ፤ እንዲያውም  ህ.ወ.ሓ.ት የሚፈጽማቸውን  ስሕተቶች የትግራይ ሕዝብ እንደሚጋራ  አድርገው የሚመለከቱም  አሉ፡፡ በመኾኑም  የድርጅቱ መጠሪያ የኾነውን  ህዝባዊ ወይኔ  ሓርነት  ትግራይ የሚለውን  ስያሜ በማሳጠር ወያኔ  እያሉ የትግራይን  ሕዝብ በሙሉ በድርጅቱ  አባልነት ይፈርጁታል፡፡ በእርግጥ ህወሓት  እና  የትግራይ  ህዝብ ቀደም ሲል ያስተሳስራቸው  ምክንያት  ነበር፡፡ በጨለማው  የደርግ ዘመን ይደርሱ የነበሩትን አፈናዎች፣ግድያዎች  እና ጥቃቶች በጋራ  መክተዋል፡፡  ግንኙነታቸው  ከፓለቲካ አልፎ የደኅንነት  እና የህልውና  ኾኖ ቆይቷል፡፡ ይህ ግንኙነት  ሊፈጥረው የሚችለውን  ሥነ ልቡናዊ ኹኔታ መገመቱ ተገቢ ነው፡፡ የፓለቲካ ድርጅት  እና ኅብረተሰብ አንድ ኾነው  እንዲታዩ ያደርጋቸዋል፡፡ ከደርግ ውድቀት ማግስት ጀምሮ  የትግራይ ሕዝብ አንዳንድ ጥያቄዎችን ያነሣ ነበር፡፡ ኾኖም  በትጥቅ ትግሉ የተፈጠረው  ጥብቅ ግንኙነት  እየጋረዳቸው  ጎልተው አይወጡም ነበር፡፡ እንዲያውም  አልፎ አልፎ የልጅ እና የወላጅ  ግንኙነት  በሚመስል ስሜታዊ ትስስር ምክንያት ጥያቄዎች  ይዳፈኑ ነበር፡፡ ህ.ወ.ሓ.ት ስህተት ቢፈጽምም

«ዞሮ ዞሮ ልጆቻችን ናቸው» የሚል አስተሳሰብ በኀብረተሳብ ዘንድ ይንጸባረቅ ነበር የትግራይ ህዝብ ጥያቄዎች ጎልተው የወጡት በኢትዮ- ኤርትራ ጦርነት ወቅት በተከሰተው ቀውስ ነበር። የኢትዮ-ኤርትራን ግንኙነት አያያዝ የትግራይ ህዝብ አይደግፈውም ነበር፤ ጦርነቱ ከተከሰተ በኋላም በጦርነት አካሄድ ላይ ጥያቄዎችን ያነሳ ነበር። ጎልቶ የወጣው ጥያቄ ይህ ይኹን እንጂ ሌሎች የፓሊሲ ጥያቄዎችም ይነሡ ነበር።

ከሁሉም በላይ በከተማ የሚኖረው ይኹን በገጠር ያለው ሕዝብ ጥየቄ ያነሳው ግን ህወሓት ከሁለት መከፈሉ በተከሰተበት ወቅት ነበር። ክፍፍሉን አስመልክቶ በሥልጣን ላይ ያለው ቡድን በአፈንጋጮች መጥፎነት ዙሪያ ማብራሪያ ለመስጠት ሲሞክር «መሰረታዊ ልዮነታችኹ ምንድን ነው? አፈንጋጮች የምትሏቸው ለምን በግንባር ቀርበው አቋማቸውን አይገልጹም? እነርሱ ሐሳባቸውን ቢገልጹ ምን የሚያስፈራችኩ ነገር አለ?...» ወዘተ የሚሉ ጥየቄዎችን ያቀርብ ነበር። ለሚያቀርባቸው ጥያቄዎች ግን ምንም ምላሽ አላገኘም ። እንዲያውም የአፈንጋጭ ወገን እየተገባለ ለወከባ እና ጫና ተጋልጣል።

በርካታ ትግራይ ተወላጆች በዚህ ሰበብ ሥራቸውን እንዲያጡና ተሸማቅቀው እንዲኖሩ ተደርገዋል። ከዚህ በኃላ ሕዝቡ ውስጥ ውስጡን የአማራጭ ያለህ ይል ጀመር።

እንዳንዶቹም ይህን ዕውን ለማድረግ እንቅስቃሴያቸውን አጠናከሩ፤ ከሁለት ዓመት በኋላ የተካሄደው የመቀሌው የመጀመሪያ ሰብሰባም የትግራይ ሕዝብ በአንድ የፓለቲካ ድርጅት ፈላጭ ቆራጭነት ለመኖር እንደማይፈልግ ያሳየበት ጽኑ የአቋም መገለጫ ነው። በእውነቱ ክሥተቱ የአማራጭ ያለህ ብሎ በድፍረት የቆመበት አጋጣሚ ነው።

2. <u>የትግራይ ሕዝብ በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች ያሉትን ችግሮች ይርራል</u>

የትግራይን ተጨባጭ ኹኔታ በሚገባ የማይገነዘብ ወገን ሌላ የተሳሳተ አስተሳሰብም ይሰነዝራል። የትግራይ ሕዝብ እጅግ የደላው፣ ኑሮው የተሳካለት እና የጠየቀውን ሁሉ የሚያገኝ አድርጎ ይመለከተዋወል። መቀሌ ላይ በተካሄደው ስብሰባ የተነሱት ጥያቄዎች እና በኢትዮ- ኤርትራ ጦርነት አካላቸው የጎደለ፣ ከሰራዊቱ ቤት በተቀናሽነት በተሰናበቱ እና ከኤርትራ የተፈናቀሉ በብዙ ሺሕ የሚቆጠሩ ወገኖች ኑሯቸው የከፈ እና የተመሰቃቀለ በመኾኑ መፍትሔ እንደሚሹ ገልጸዋል።

ከእነዚህ በቀጥታ የጦርነቱ ገፈት ቀማሽ ከኾኑት ወገኖች በተጨማሪ ኀብረተሰቡ የብልሹ አስተዳደር፣የሙስና እና አድልዎ ስለባ መኾኑንም በይፋ ገልጧል።

የመንግስት ሰራተኛ የሥራ ምደባ ፓለቲካዊ ወገናዊነትን መሰረት ማድረጉ ታማኝ የሚባሉ ወገኖች በሌሉበት እንኳ የሥራ ድልድል እንደሚደርግላቸው ይገልጻል፡፡ ተማሪዎች ሳይቀሩ ሥራ የሚያገኙት በትምህርት ውጤታቸው ሳይኾን በአባልነታቸው መኾኑ በምሬት ገልጸዋል፡፡ አርሶ አደሩ የዕለት ጉርሱን ከሚሚላት አልፎ የሚመገበው እያመረጠ ነው ተብሎ በሚነገርበት ወቅት ለከፋ ችግር የመጋለጡ እሮሮ ተሰማቷል፡፡ ያለበቂ ዋስትና ከመሬቱ እንደሚፈናቀል፣ ለቀበሌ አስተዳደሮች ብልሹ እና አድሏዊ አመራር መዳረጉ፣ ከዚያም አልፎ በረኀብ አለንጋ መገረፉ ተነግሯል፡፡ ጩኸቱን ለማስማት የት መሄድ እንዳለበትም ግራ ተጋብቷል፡፡ ለ20 ቀናት ይጠየቅ የነበረውን የነጻ ሥራ አገልግሎት ወደ 40 ቀናት ከፍ ማለቱንም በምሬት ይገልጻል፡፡

በአጭሩ ትግራይ ሕዝብ በኢትዮጵያ ውስጥ በሌላው ወገኑ ላይ የሚደርሱትን በደሎች እና ችግሮች እንደሚደርስበት ተገልጻል፡፡ ምናልበት ከትግራይ ሕዝብ ውስጥ የደላው ቢኖር ከአንድ በመቶ በታች የኾነው የመንግሥትን ሀብት ያለአግባብ ተጠቃሚ የኾነው እና ለባለስልጣናቱ የቀረቡ ጥቂት ነጋዴዎች ብቻ መኾናቸው ተመልክቷል፡፡ ነጋዴዎች ቢኾኑም ከሌላው የአገሪቱ ክፍል በተለየ የግብር እና የቀረጥ ጫና እንደሚደርስባቸው ይናገራሉ፡፡

የትግራይ ሕዝብ ከማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አስተዳደራዊ ኀይሎች ሌላ በፓለቲካዊ መስም ከፍተኛ ችግር እንደሚደርስበት በጻፉቸው አስተያየቶች ገልጸል፡፡ ክልሉ የአንድ ፓርቲ አገዛዝ ብቻ የሰፈነበት በመኾኑ ምርጫ የይስሙላ እንጂ አማራጭ ፓሊሲዎች ቀርበውለት እንደማካሄድ ይገልጻል፡፡ በዚህ ረገድ ከሌሎች ክልሎች ጋር ሲነጻጸር ወደ ኋላ እንደቀረም ይናገራል፡፡ በአንድ ፓርቲ አገዛዝ ሥር ስለሚገኝ ደግሞ ዴሞክራሲያዊ አማራጮች እና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹ እንደማይከበሩለት ይናገራል፡፡ የትግራይ ሕዝብ በዚህ ረገድ ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይብስ እንደ ኾነ እንጂ እንደሚይሻል ታውቋል፡፡

3. <u>ሰላማዊ እና ሕጋዊ ትግል ከባድ ቢኾንም የሚቻል ነው!!</u>

ሌላው አከራካሪ ጉዳይ አሁን ባለው ፓለቲካዊ ምኅዳር ሕጋዊ እና ሰላማዊ ትግል ማድረግ አይቻልም የሚል ነው፡፡ በእርግጥ የአገራችን ፓለቲካዊ ማኅዳር እጅግ አስቸጋሪ መኾኑ የታወቀ ነው፡፡ በሕገ መንግሥቱ የሰፈሩትን የዜጎች መብቶች

ተግባራዊ ማድረግ እጅግ ከባድ ቢሆንም በዚህ አስቸጋሪ የፓለቲካ መልክአ ምድርም ጭምር መሞከሩ ተገቢ መኾኑን የመቀሌው ስብሰባ አመልካች ኾኗል።
በመቀሌ የተካሄደው ሕዝባዊ ስብሰባ እጅግ አስቸጋሪ የኾነውን ሕጋዊ ትግል አንድ ገጽታ ነው። የትግራይ አካባቢ ከሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች የከፋ የነጻነት ችግር ይኖረው እንደ ኾነ እንጂ የተሻለ ሊኾን አይችልም። ከሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢዎች በላይ የኢሕአዴግ አባላት በብዛት የሚገኙበት፣ የአንድ ፓርቲ አገዛዝ ከ30 ዓመታት በላይ የሰፈነበት፣ከመጠን በላይ የደኅንነት፣ የፓሊስ፣የሚልሻ እና የመደበኛ ጦር ብዛት ያለበት፣የአንድ ፓርቲ አባላት ከክልል እስከ ቤተሰብ ድረስ ኅብረተሰቡን የተቆጣጠሩበት፣በአመለካከት ደረጃ የህወሓት/ኢህወዴግ ቤዝ ዓምባ ተደርጎ የሚታይበት ነው። በዚህ አካባቢ ሰላማዊ እና ትግል ለማድረግ ከተቻለ በሌላው አካባቢም እውን የማይኾንበት ምክንያት አይኖርም። ዋናው ነገር ግን የህዝቡን ፍላጎት ተከትሎ ከሐዝቡ ጋራ አብሮ መሥራት ነው።
በዚህ አጋጣሚ የሥርዐቱ ጫና ሳይበግራቸው ባደረግነው ሕዝባዊ ሰብሰባ የተገኙትን ሁሉ ልናመሰግን እንወዳለን፤ ለወደፊቱም በምናደርጋቸው ስብሰባዎች የተለመደ ትብብራቸውን እንዲያደርጉልን ጥሪያችንን እናቀርባለን።

(*አቶ ገብሩ ዐሥራት የዓረና ትግራይ ለዴሞክራሲ እና ለሉዓላዊነት ፓርቲ ሊቀ መንበር ናቸው።)